# 2.3 የፕሮጀክት ማመልከቻ ግምገማ (Appraisal)



## " ወዴት እንደምትሄድ ካላወቅክ ሁሉም መንገዶች የትም ሊወስዱህ ይችላሉ::"

## እንዲሁም

## "ፕሮጀክትህን ወዴት አቅጣጫ መጓዝ እንደአለበት ካላሳየከው በማንኛውም አቅጣጫ ሊጓዝ ይችላል::"

## ነገር ግን

## " በዘላቂነት መንገድ ብቻ አንዲጓዝ ከፈለግክ የፕሮጀክት ሀሳቡን ገምግመው::"

## 1. የፕሮጀክት ማመልከቻ ግምገማ (Appraisal)

➢ ማመልከቻውን የተቀበለው ግለሰብ ፋይል ከከፈተለት በኋላ የሚቀጥለው ሁደት ማመልከቻውን በቢሮና በመስክ ደረጃ መገምገም (Appraisal) ነው ::

**የፕሮጀክት ግምገማ (Project appraisal) ማለት**

**አንድ የፕሮጀክት ሀሣብን/ማመልከቻን ለዚሁ ምዘና እንዲሆኑ ከተዘጋጁ መስፈርቶች አንፃር ብቁ መሆኑንና አለመሆኑን መመዘን ማለት ነው::**

- **ለግምገማ የሚቀመጡት መመዘኛ ነጥቦች የፕሮጀክቱን ዘላቂነት በማረጋገጥ ላይ ያተኮሩ ናቸው ::**
    - በዚህም ምክንያት የግምገማ ዋናው አስፈላጊነት የፕሮጀክቱ ዘላቂነት ላይ አስተዋጽኦ ያላቸውን ወሳኝ መስፈርቶችን የፕሮጀክት ሃሳቡ ማሞላቱን/ሊያሟላ እንደሚችል ለማረጋገጥ ነው::
    - በአንዳንድ ፅሁፎች፣ የፕሮጀክት ግምገማ ሪፖርቶችና ግለሰቦች እንደሚገልፁት በደንብ የተገመገመ ፕሮጀክት ከወዲሁ የዘላቂነት መንገድን ያጋመሰ እንደሆነ ይገልፃሉ::
    - በተጻጻሪ ሁኔታ ደግሞ አንዳንዶች የፕሮጀክት ማመልከቻ ግምገማ የፕሮጀክት ሀሳብን ላለመቀበል የሚደረግ ማቅማማት አድርገው የሚወስዱ አሉ::

- የፕሮጀክት ግምገማ አስፈላጊነት ስለሚታመንበት ከማ.ፐ.ት የበጀት ድጋፍ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በቢሮና በመስክ ደረጃ የገመገማሉ::

- በቢሮና በመስክ ደረጃ የፕሮጀክት ማመልከቻዎችን ግምገማ ለማከናወን የሚጠቅሙ ቅጾች ተዘጋጅተዋል::

## 1.1 በቢሮ ደረጃ የሚደረግ ግምገማ (Desk Appraisal)

- ***ይህ ግምገማ የሚከናወነው ማመልከቻውን በተቀበለው ግለሰብ ሁኖ ማመልከቻውን ወዲያውኑ እንደተቀበለና አመልካቾች ባሉበት ነው:: ይህም እንዲሆን የተደረገው አመልካቾች:-***
  - *ማመልከቻው ላይ ያልተሟላ ነገር ካለ ተለይቶ እንዲያሟሉ ወዲያውኑ ለመግለጽ፣*
  - *የማመልከቻቸውን ሁኔታ ወዲያው አውቀው ለሚቀጥለው ሂደት ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግና፣*
  - *ለዚሁ ጉዳይ ብዙ ግዜ የተመላለሱ ግዜያቸውን እንዳይባክን ነው::*

- ***በቢሮ የሚደረገው ግምገማ በሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው::***
  1. *ማመልከቻው በትክክል መሞላቱንና መያያዝ የሚገባቸው ሌሎች ሰነዶች መያያዛቸውን ማረጋገጥ፣*
  2. *በቢሮ ደረጃ መታየት የሚገባቸው አንዳንድ መመዘኛዎችን ያሟላ እንደሆነ መፈተሽ ናቸው::*
  - *ለቢሮ ደረጃ ግምገማ የሚጠቅሙ ዝርዝር የመመዘኛ ነጥቦች በግምገማ ቅፁ ላይ ተቀምጠዋል::*
  - *ለናሙናነት የተዘጋጀውን በቢሮ ደረጃ የተደረገ ግምገማን በዚህ የስልጠና መመሪያ <u>በቅጽ ዝ.3</u> ላይ ይመልከቱ::*

- *በቢሮ ደረጃ ግምገማ ያደረገው ግለሰብ ከግምገማው በተገኘው ውጤት መሰረት* ***የፕሮጀክት ማመልከቻ መቀበልንና በቢሮ ደረጃ የተደረገ የግምገማ ውጤትን መግለጫ*** *<u>በቅጽ ዝ.4</u> ላይ ከሚከተሉት ሦስት ይዘቶች አንዱን በመምረጥ ማመልከቻውን ላመጣው የዋ.ሽ.ኮ አባል ይሰጣል::*
  1. *ማመልከቻው የቢሮ ደረጃ ግምገማውን ማለፉንና ከተቻለ የመስክ ግምገማ የሚከናወንበትን ጊዜያው ቀን መግለጽ:: የመስክ ግምገማ ቀኑ ማመልከቻውን ካስረከበው የዋ.ሽ.ኮ አባል ጋር መስማማት ያስፈልጋል::*
  2. *ማመልከቻው ገልጽ ባለመሆኑም ሆነ ባለመሟላቱ የተሟላ ግምገማ ማድረግ ካልተቻለ ማሟላት የሚገባቸውን በደብዳቤ በመግለጽ ማመልከቻውን መመለስ::*
  3. *ማመልከቻው የተሟላ ሁኖ ግን በቢሮ ደረጃ የተደረገው ግምገማ ለበጀት ድጋፍ ብቁ የማያረገው ከሆነ ተቀባይነት አለማግኘቱን ከነምክንያቱ መግለጽ ይሆናሉ:: በዚህ ጊዜ ማመልከቻው አይመለስም::*

## የገጠር መጠጥ ውሃ ጣቢያዎች ማመልከቻዎችን በቢሮ ደረጃ መገምገሚያ ቅጽ (ዝ.3)

1. የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥር (በውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የሚሰጥ) : ደወ/06/2003
2. የአመልካች ማህበረሰብ ስም: ልጀ ንጉስ
3. አድራሻ
   - ዞን : ምዕራብ ጎጃም
   - ቀበሌ : ንጉስ
   - ወረዳ : ደጋ ዳሞት
   - ጎጥ : ልጀ ንጉስ
4. ማመልከቻው የቀረበበት ቀን : ህዳር 17/2003 ዓ.ም
5. የቢሮ ደረጃ ግምገማው የተደረገው ህዳር 17/2003 ዓ/ም
6. የቢሮ ደረጃ የግምግማው ውጤት:-

■ የቢሮ ደረጃ ግምገማወን ስላለፈ የመስክ ግምገማ ማካሄድ ያስፈልጋል

☐ የቢሮ ደረጃ ግምገማውን ለማከናወን ከዚህ በታች የተዘረዘረው/ሩት ተጨማሪ መረጃ/ዎች ያስፈልጋል/ጋሉ::

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

______________

☐ በቢሮ ጀረጃ በተደረገው ግምገማ መሰረት ማመልከቻዉ ተቀባይነት አላገኘም::

ምክንያቱም/ቶቹም------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------::

## በቢሮ ደረጃ መገምገሚያ መሰስፈርቶችና የግምገማ ውጤት

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የተጠየቀው የውሃ ጣቢያ ግንባታ ዓይነት በማ.ፐ.ት የሚደገፍ ነው ወይ?<br>ሀ. የእጅ ጉድጓድ ለ. በስበት ሀይል የሚሠራ ምንጭ በቦታው<br>ሐ. በስበት ሀይል የሚሠራ ምንጭ ከነማጠራቀሚያ ጋኑ በቦታው<br>መ. ሎሎች አነስተኛ ቴክኖሎጂዎች /ዓይነቱ ይጠቀስ/ ------------------------------------------------ | X | |
| 2 | አዎ ከሆነ፣ ከላይ የተጠቀሱትን ፕሮጀግቶች የሚወክለውን አንዱን ፊደል ይጻፉ:: | ሀ | |
| 3 | ሁሉም አመልካቹ ማህበረሰብ የፕሮጀክቱ ግንባታ እስኪጀመር ድረስ የግል መጸዳጃ ቤት ለመገንባት ቃል ገብቷል ወይ? | X | |
| 4 | ከማ.ፐ.ት የተጠየቀው የገንዘብ መጠን ለወረዳው ከተቀመጠው የአንድ ፕሮጀክት የበጀት ጣሪያ ውስጥ ነው ወይ? ጣሪያው የተወሰነ ከሆነ ብቻ:: | X | |
| 5 | የህብረተሰብ ተሳትፎ ወደ ገንዘብ ተለውጦ ከጠቅላላው የበጀት መጠን ቢያንስ 15 በመቶ ይሆናል ወይ? | X | |
| 6 | ማመልከቻው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች ይዟል ? | አዎ | የለም |
| 6.1 | ስለውሃ ጣቢያው አስፈላጊነት ህብረተሰቡ የተወያየበት አጀንዳና ቃለ ጉባኤ ላይ የሚከከተሉት ተካተዋል ወይ? | | |
| | • የውሃ ጣቢያ ግንባታው በትክክል የሁሉም ማህበረሰብ አባላት ፍላጎት መሆኑን ማረጋገጫ (በስብሰባ ላይ የተገኙ ተጠቃሚ የህብረተሰብ አባላት ስም ዝርዝር ከነፊርማቸው):: | X | |
| | • ተጠቃሚው ህብረተሰብ በጉልበት በአካባቢ ቁሳቁስና በጥሬ ገንዘብ ለማዋጣት የተገባ ቃል:: | X | |
| | • የዋ.ሽ.ኮ አባላት ስም ዝርዝር በዕድሜና በሥራ ድርሻ | X | |
| 6.2 | በህብረተሰቡ ገንዘብ ተዋጥቶ በገንዘብና ቁጠባ ተቋም በቁጠባ ሂሣብ ተቀማጭ መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ | X | |
| 6.3 | ከቀበሌ አስተዳደር የድጋፍ ደብዳቤ | X | |
| 7 | ማመልከቻው መስፈርቶችን አሟልቶ ለመስክ ግምገማ ብቁ ነው? | X | |
| 8 | ማመልከቻው መስፈርቶችን ማሟላት ካልቻለ ለአመልካቾች ከነምክንያቱ ተገልፆላቸዋል? | | |
| 9 | የግምገማው ውጤት ለአመልካቾች የተገለፀበት ቀን: <u>ህዳር 17/2003</u> | | |

<u>ግምገማውን ያካሄደው ባለሙያ</u>

ሥም :____________________ ፊርማ: _____________________ ቀን : <u>ህዳር 17/2003</u>

## ቅጽ - ዝ.4
## ለመጠጥ ውሃ ተቋም ግንባታ የፕሮጀክት ማመልከቻ መቀበልንና በቢሮ ደረጃ የተደረገ ግምገማ ውጤትን መግለጫ ቅጽ/Acknowledgement of receipt of application and informing the result of desk appraisal for a water point application/

**የአመልካቹ ማህበረሰብ መጠሪያ ስም : ልጀ ንጉስ**

**ዞን : ምዕራብ ጎጃም** **ቀበሌ : ንጉስ**

**ወረዳ : ደጋ ዳሞት** **ጎጥ : ልጀ ንጉስ**

ከዚህ በታች በተገለፀው ቀን ከወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ለውሃ ጣቢያ ግንባታ የበጀት ድጋፍ ጥያቄ ማመልከቻ ቅፅ አቅርበዋል፡፡ የቀረበው ማመልከቻ በቢሮ ደረጃ ከተገመገመ በኋላ፡-

[x] ማመልከቻው ማሟላት የሚገባቸውን መረጃዎች ሁሉ አሟልቷል፣ በቢሮ ደረጃ የሚታዩ መመዘኛዎችን አልፏል፡፡ ስለዚህ ከአመልካቾች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የመስክ ግምገማ /Field Appraisal/ የሚከናወንበት ቀን ህዳር **28/2003 ዓ.ም** ይሆናል፡፡

[ ] የቀረበው ማመልከቻ መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች ያላሟላ በመሆኑ በቢሮ ደረጃ የሚደረገውን ግምገማ በተሟላ ሁኔታ ማከናወን አልተቻለም፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ማመልከቻውን እንዲያስተካክሉና የጎደለውን መረጃ እንዲያሟሉ ማመልከቻቸው ተመልሶላቸዋል፡፡ በማመልከቻው ላይ የጎደሉና መሟላት የሚገባቸው መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

[ ] በቢሮ ደረጃ / Desk Appraisal / በተደረገው ግምገማ መሠረት የኘሮጀክት ማመልከቻው ከማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ የበጀት ድጋፍ ተቀባይነት አለማግኘቱን እንገለፃለን፡፡ ማመልካቻው ተቀባይነት ያለማግኘቱ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**ስም : መክብብ ሰለሞን** **ፊርማ ________________** **ቀን : ህዳር 17/2003**

***ማሳሰቢያ***

1. ማመልከቻው በቢሮ ደረጃ ከታየ በኋላ የማመልከቻው ሁኔታ ከሦስቱ ሳጥኖች አንዱ ላይ ምልክት ይደረግ፡፡
2. ስምና ፊርማ የሚሉት ክፍት ቦታዎች የሚሞሉት በወረዳው ዋሽ ቡድን ማመልከቻዎችን ለመቀበልና በቢሮ ደረጃ ግምገማ /Desk Appraisal/ እንዲያከናውን ሀላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ወይም የወረዳው ጽ/ቤት ሀላፊ ነው፡፡ ይህ ፎርም በሁለት ኮፒ ተሞልቶ አንደኛው ለአመልካቹ ወዲያውኑ ሲሰጥ ሌላው ለፕሮጀክቱ ለማመልከቻው ፋይል ተከፍቶለት ይቀመጣል፡፡

## 1.2 በመስክ ደረጃ የሚደረግ ግምገማ (Field Appraisal )

- **በመስክ ደረጃ የሚደረገው ግምገማ ጥቅም ማመልከቻ የቀረበለት የውሃ ጣቢያ በሚገኝበት ቦታ ድረስ በመሄድ:-**
    - በማመልከቻው ላይ የተቀመጡትን መረጃዎች ተክክለኛነት ለማረጋገጥ እና
    - ከአመልካች ማህበረሰቡ አባላትና ሌሎች መረጃ ሊሰጡ ከሚችሉ ግለሰቦች/ተቋማት ጋር በመወያየት በመስክ ደረጃ ለመገምገሚያነት ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር ጥያቄ የቀረበለት ፕሮጀክት ሊተገበር የሚችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመመዘን ነው::

- **የመስክ ግምገማ የሚከናወነው የተለያዩ ሙያ ባላቸው ከሁለት ባላነሱ ቢቻል በ3 የወረዳ ባለሙያዎች ነው::**
    - በወረዳው የውሀ ሀብት ልማት ጽ/ቤት አግባብ ያለው ባለሙያ እጥረት ከሌለ በስተቀር የመስክ ገምጋሚዎች የቡድኑ ባለሙያዎች መሆን አለባቸው::
    - የባለሙያ እጥረት በሚኖርበት ወቅት ከወረዳው ከሚገኙ ከሌሎች የዋ.ሽ ሴክተር ጽ/ቤቶች ባለሙያዎችን መጠቀም ይቻላል::
    - ከመስክ ደረጃ ገምጋሚው ቡድን አባላት ውስጥ ቢያንስ አንዱ/ዷ በውሃ ጣቢያ ቦታ መረጣ የቴክኒክ ልምድና እውቀት ያለው/ላት መሆን ሲኖርበት/ባት አንደኛ ው/ዋ ደግሞ በስርዓተ ጾታ፣ በህብረተሰብ ተሳትፎና የመሳሰሉትን መመዘኛዎች ሊገመግም የሚችል/የምትችል ባለሙያ መሆን አለበት/ባት::
    - የወረዳው የማ.ፕ.ት ተቆጣጣሪ (CMP supervisor) የመስክ ገምጋሚው ቡድን አባል ነው::
    - አቅም እስከፈቀደ ድረስ የመስክ ግምገማው የፕሮጀክት ማመልከቻውን ከአመልካቾች በተቀበለ በ 15 ቀናት ውስጥ መከናወን ይኖርበታል::

- **በቢሮ ደረጃ ተገምግሞ ተቀባይነት ያገኘ የፕሮጀክት ማመልከቻ በመሥክ ደረጃ ከሚከተሉት ዋና ዋና መስፈርቶች አንፃር ይገመገማል:: እነዚህም የመገምገሚያ መጠይቆች ለመስክ ግምገማ በተዘጋጀው ቅፅ በማ.ፕ.ት የተግባር መመሪያ <u>በቅጽ ዝ.5</u> ላይ ተቀምጠዋል::**
    - ➢ ጥያቄ የተቀረበለት ፕሮጀክት የማህበረሰቡ ዋነኛ ችግር መሆኑን ፣
    - ➢ ፕሮጀክቱ ከሚኖረው የማህበራዊ ዘላቂነት አንፃር፣
    - ➢ ከህብረተሰብ ተሳትፎ አንፃር፣

- ከቴክኒካዊ መመዘኛዎች አንፃር (ከውሃ ጣቢያ ቦታ መረጣ ቴክኒካዊ መመዘኛ ዎች አንጻር)፣
- ከአካባቢያው ዘላቂነት አንጻር፣
- ፕሮጀክቱ የሴቶችን የሥራ ጫና ከመቀነስና ከሴቶች ተሳትፎ አንጻር፣
- ተጠቃሚዎች ለፕሮጀክቱ ዘላቂነት የሚያስፈልገውን የኦፕሬሽንና ጥገና ወጪ ከመሸፈን አቅምና ፍላጎት አንፃር ናቸው፡፡

- ለናሙናነት የተዘጋጀውን በመስክ ደረጃ የተደረገ ግምገማን <u>በቅጽ ዝ.5</u> ይመልከቱ፡፡
- በመስክ ግምገማ ወቅት ገምጋሚው ቡድን የፕሮጀክት ሀሣቡን ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና መመዘኛዎች ከመገምገም በተጨማሪ አስፈላጊ ከሆነ፡-
  - የፕሮጀክት ማመልከቻው ላይ መስተካከል /መሻሻል/ የሚያስፈልጋቸው ነገሮችን ያሻሽላል፣
  - በፕሮጀክት ማመልከቻው ላይ የተጠየቀውን በጀት ይከልሳል፣
  - በህዝቡ የተመረጠው የውሃ ጣቢያ መገንቢያ ቦታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል ካስፈለገም እንደገና ይመርጣል፣
  - ማመልከቻው ላይ ከላይ የተጠቀሱትና መሰል መሻሻሎች አስፈላጊ ከሆኑና ከተደረጉ ግምገማው የሚካሄደው በተሻሻለው ማመልከቻ ላይ ይሆናል፡፡

- አመልካቹ ማህበረሰብ በፕሮጀክት ማመልከቻው ላይ ለማዋጣት ቃል የገባውን የገንዘብ መዋጮ በአጠቃላይ ሰብስቦ በገንዘብና ቁጠባ ተቋም በማስቀመጥ ደረሰኙን ያላቀረበ ከሆነ የመስክ ግምገማው እንደተከናወነ ገምጋሚው ቡድን የግምገማው ውጤት የፕሮጀክት ሃሳቡን ተቀባይነት ሊያስገኘው የሚችል መሆኑን ከወሰነ ለአመልካቾች ማመልከቻው የመጨረሻ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ቃል የገቡትን ገንዘብ በሙሉ ሰብስበው በገንዘብና ቁጠባ ተቋም በማስቀመጥ ደረሰኙን ማቅረብ እንዳለባቸው፣ ይህ ካልሆነ ግን የፕሮጀክቱ ግምገማ እንዳልተጠናቀቀ በመስክ ግምገማው ወቅት መንገር አለባቸው፡፡

- ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና መመዘኛዎች በመስክ ደረጃ ግምገማ የተካሄደለት ማመልከቻ ውጤቱ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-
  - ለበጀት ድጋፍ ተቀባይነት ያለማግኘት (Rejection) ወይም
  - በመስክ ግምገማው ቡድን ተቀባይነት ካገኘ ለመጨረሻ ውሣኔ (Approval) ለወረዳው የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ቡድን /ዋሽ ቲም/ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
- በመስክ ደረጃ በተደረገው ግምገማ ምክንያት ለበጀት ድጋፍ ተቀባይነት ያላገኘ የፕሮጀክት ማመልከቻ ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት በመግለፅ ለአመልካቹ

ማህበረሰብ በወረዳው የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ቡድን /ዋሽ ቲም/ ሰብሳቢ በሚጻፍ ደብዳቤ ይገለፅለታል::

## 1.3 የመስክ ግምገማ ውጤት ሪፖርት ዝግጅት

- በግምገማው ወቅት የተገኙትን ውጤቶች በመገምገሚያ ቅጹ ላይ ማስፈር፣
- የግምገማ ውጤቱን ከማ.ፕ.ት የበጀት ድጋፍ ለማግኘት ወሳኝ ከሆኑት መስፈርቶች ጋር ማነጻጸር፣
- በግምገማ ውጤቱ መሰረት ሪፖርቱን ማጠናቀቅና ይህንንም ለወረዳው ወረዳው የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ቡድን /ዋሽ ቲም/ የመጨረሻ ውሳኔ መስጫ/ማጽደቂያ ፎርምን በመሙላት ለቡድኑ ለውሳኔ ማቅረብ::
- ይህ ስራ በዋነኛነት የሚሰራው በወረዳው ማ.ፕ.ት ተቆጣጣሪ ይሆናል::

## የገጠር መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ማመልከቻዎችን በመስክ ደረጃ መገምገሚያ ቅፅ

## (ዝ.5)

የገምጋሚ ቡደን አባላት ቁጥር 3 ቢሆን ተመራጭነት ያለው ሲሆን መሀንዲስ ወይም ጆኦሎጂስት ከወረዳው የውሃ ሀብት ልማት ቡድን ቢኖር ይመረጣል::

**1. አጠቃላይ**

ሀ. የአመልካች ማህበረሰብ ስም : <u>ልጀ ንጉስ</u>

ለ. ሊገነባ የታሰበው የውሃ ተቋም ዓይነት : <u>ከ 15 ሜትር ጥልቀት ድረስ ሊቆፈር የሚችል የእጅ ፓምፕ የሚገጠምለት የእጅ ጉድጓድ</u>

ሐ. በውሃ ጣቢያው ተጠቃሚ ህዝብ ብዛት

- አባውራ/ ማውራ : **<u>55</u>**
- ጠቅላላ ተጠቃሚ : **<u>270</u>** ወንድ : **<u>132</u>** ሴት : **<u>138</u>**

መ. በመስክ ግምገማ ወቅት ቡድኑ ያነጋገራቸው

- የዋ.ሽ.ኮ አባላት ቁጥር : **<u>4</u>**
- የተጠቃሚ አባላት ቁጥር : **<u>68</u>**
- የቀበሌ አስተዳደር አባላት ቁጥር : **<u>4</u>**

**2. ማህበራዊ ተቀባይነት**

| ተቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| ሀ | የዋ.ሽ.ኮ አባላት ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ተመርጠዋል? የምርጫውን ሂደት ገምግም:: | x | |
| ለ | የተጠቃሚ ህብረተሰብ አባላት በተለያዩ የፕሮጀክቱ ዑደት ተሳትፎ | አዎ | የለም |
| ለ.1 | ተጠቃሚዎች በፍላጎት ቅደም ተከተል አወጣጥ ላይ ተሳትፈዋል? | x | |
| ለ.2 | ፕሮጀክቱ የህብረተሰቡ ቅድሚያ ፍላጎት ነው ወይ? | x | |
| ለ.3 | ተጠቃሚዎች በቦታ መረጣና በፕሮጀክት ዲዛይን ተሳትፈዋል? | x | |
| ለ.4 | ተጠቃሚዎች በሥራ እንቅስቃሴው ለመሳተፍ ተነሳሽነት አላቸው? | x | |
| ለ.5 | ተጠቃሚዎች የውሃ ጣቢያውን ለማስተዳደርና ለመጠገን ቁርጠኝነት አላቸው? | x | |
| ሐ | ለውሃ ጣቢያ ግንባታ የተመረጠው ቦታ ከባህልና ከሀይማኖት አንፃር በህብረተሰቡ ተቀባይነት አለው? | x | |
| መ | ለውሃ ጣቢያ ግንባታ በተመረጠው የቦታ ባለይዞታ ጋር ስምምነት ተደርሷል? | x | |

**3. ቴክኒካዊ አዋጭነት/ተቀባይነት**

ሀ/ ህብረተሰቡ በአሁኑ ሰዓት የሚጠቀምበትን ውሃ ከየት ያገኛል?

<u>በአቅራቢያው ከሚገኝ ወንዝ::</u>________________________________

_______________________________________________

ለ/ ህብረተሰቡ በአሁኑ ሰዓት የሚጠቀምበት ተሻሽሎ የተገነባ የውሃ ጣቢያ በቅርብ ርቀት ይገኛል?

አዎ ☐ የለም ■

መልሱ አዎ ከሆነ፣ ምን ዓይነት የውሃ ጣቢያና በአማካይ በምን ያክል ርቀት ላይ ይገኛል? የውሃ ጣቢያው ዓይነት ______________________

አማካይ የአንድ ጉዞ በደቂቃ __________ በኪሎ ሜትር ________

ሐ/ ሊገነባ የታቀደው የውሃ ጣቢያ በቂ ውሃ ከማግኘትና ለግንባታ ካለው ምቹነት አንፃር ተቀባይነት አለው? አዎ ■ የለም ☐

መ/ በህብረተሰብ የተመረጠው የመጠጥ ውሃ ተቋም መገንቢያ ቦታ ከውሃ ጣቢያ/ከቦታ/ መምረጫ መስፈርቶች አንፃር ተቀባይነት ከሌለው ሌላ የተሻለ ቦታ ከህብረተሰቡ ጋር በመመካከር መመረጥ ያለበት ሲሆን ይህም የቦታ መረጣ ሪፖርት ከግምገማ ሪፖርት ጋር አብሮ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።

ሠ/ ሥራውን ማከናወን የሚችሉ የግል ተቋራጮችን/አርቲዣኖችን በአካባቢው/በወረዳው ማግኘት ይቻላል?

አዎ ■ የለም ☐

ከሌሉ ሌላ ምን አማራጭ መፍትሄ አለ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**4. ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያለው ተቀባይነት**

ሀ/ በፕሮጀክቱ ዲዛይን የአጥር፣ የፍሣሽ ማጠንፈፊያና ማስረጊያ እንዲሁም ሌሎች የመከላከያ ሥራዎች ተካተዋል? ካልሆነ መወሰድ ስላለበት የመፍትሄ ሀሳብ ይብራራ።

<u>ተካተዋል።</u>_______________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ለ/ የሚገነባው የውሃ ጣቢያ ለእንስሳት አገልግሎት ይሰጣል? ካልሰጠ ሌላ ምን አማራጭ ስቧል? <u>አይሰጥም ምክንያቱም በቅርብ ርቀት ወንዝ ስላለ ከዚያ ስለሚጠቀሙ።</u>_____

_______________________________________________

ሐ/ ምን ያህሉ የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ቤተሰቦች የመጸዳጃ ቤት ገንብተዋል? <u>**15ቱ**</u> ያልገነቡት እስከመቼ ገንብተው ያጠናቅቃሉ? <u>የውሃ ጣቢያው ግንባታ ከመጠናቀቁ በፊት</u>

### 5. ከሥርዓተ ፆታ አንፃር ፕሮጀክቱ ያለው ጠቀሜ

| ተቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| ሀ | ሴቶች በፕሮጀክቱ ዑደት ተሳትፎ አላቸው/ይኖራቸዋል?<br>➢ በፍላጎት ምርጫ<br>➢ በዲዛይን ዝግጅትና ቦታ መረጣ<br>➢ በግንባ ወቅት<br>➢ በአስተዳደርና ጥገና | x | |
| ለ | ሴቶች በዋ.ሽ.ኮ ቢያንስ 60 በመቶ (ቢያንስ 3 አባላት) ውክልና አላቸው? ይብራራ::__________ | x | |
| ሐ | የውሃ ጣቢያው ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የሴቶች የስራ ጫና ይቀንሳል? ይብራራ: <u>ለንጹህ ውሃ ፍለጋ ያባክኑት የነበረውን ጊዜ ስለሚቆጥብ</u>__________ | x | |

### 6. የፕሮጀክቱ ዘላቂነት

ተጠቃሚዎች የውሃ ጣቢያውን አስተዳደርና ጥገና ወጭ እንዴት ለመሸፈን እንደተስማሙ ገምግም:: ይህም እያንዳንዱ ተጠቃሚ ምን ያክል ገንዘብ በምን ያክል ጊዜ እንደሚያዋጣና የውሃ ጣቢያውን ጥበቃና ንፅህና አጠባበቅ ወጭ እንዴት ለመሸፈን እንደታሰበ ይገለፅ::

<u>**ተጠቃሚው ማህበረሰብ በዓመት ለአጠቃቀምና ጥገና ወጪ የሚሆን ብር 1000 ለማዋጣት ስምምነት ላይ ተደርሷል:: ለዚህም በተለያዩ ምክንያቶች የመክፈል አቅማቸው ደካማ ነው ተብሎ በህብረተሰቡ ከመነባቸው 5 ቤተሰቦች ውጭ 50 ቤተሰብ እያንዳንዱ ቤተሰብ በዓመት 20 ብር ለመክፈል ሲስማሙ ገንዘቡም በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል:: ለመጠቃምና ጥገና ከሚዋጣው ገንዘብ ውስጥ በወር 30 ብር ዘበኛ ለመቅጠርና ዘበኛውም የውሃ ጣቢያውን ንጽህና እንዲጠብቅ ይደረጋል::**</u>

- ለዚሁ አገልግሎት ከማህበረሰቡ በቅድሚያ የተዋጣና በባንክ የተቀመጠ የብር መጠን <u>**1000**</u>

### 7. የዋ.ሽ..ኮው ፕሮጀክቱን የመፈፀም አቅም

የዋ.ሽ..ኮ አባላት ፕሮጀክቱን በአግባቡ ለመፈፀምና ለማስተዳደር ማግኘት ስላለባቸው ስልጠና/እገዛ አስተያየት ስጥ::

<u>**የፕሮጀክቱን ግንባታና እንዲሁም ከተገነባ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ለማስተዳደር የሚያስችሉ ስልጠናዎችንና በተለይ በግንባታ ወቅት የቅርብ ክትትልና የሙያ እገዛ ይፈልጋሉ::**</u>____

______________________________

## 8. የፕሮጀክቱ የአፈፃፀም/የትግበራ ጊዜ ሰሌዳ

ለሁሉም የፕሮጀክቱ ተዋናይ ወገኖች ተስማሚ የሆነና ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችል የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ይቅረብ

| ተ.ቁ | የሥራ ዝርዝር | የ 2003 በጀት ዓመት ወራት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ነ | መ | ጥ | ሀ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሠ |
| 1 | የቅድመ ዝግጅት ሥራ /እስከ የገንዘብ ውል ስምምነት መፈራረም/ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የዋ.ሽ.ኮ ስልጠና | | | | | | | | | | | | |
| 3 | የተቋራጭ መረጣና የግንባታ ውል መያዝ | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የግንባታ ሥራ | | | | | | | | | | | | |

## 9. የተጠቃሚ ህብረተሰብ አስተዋጽኦ

በህብረተሰብ አስተዋፅኦ የሚቀርበቡትን የአካባቢ ግንባታ ቁሳቁሶችና ጉልበት መጠን ለእያንዳንዱ አስተዋፅኦ ዓይነት በአካባቢው ባለው ወይም ከወረዳው ውሃ ጽ/ቤት ከሚገኘው ነጠላ ዋጋ በማባዛት ዝርዝሩ ሰ.1 እና ሰ.2 ላይ በታዩት ሰንጠረዦች ተሰርቶ እንደሚከተለው መጠቃለል/መከለስ አለበት::

| ተቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | |
|---|---|---|
| 1 | የህብረተሰብ አስተዋጽኦ በገንዘብ ሲተመን /ጠቅላላ/ | ብር = 13242 |
| 1.1 | የሚቀርቡ የአካባቢ የግንባታ ቁሳቁሶች | ብር = 1599 |
| 1.2 | የህብረተሰቡ የጉልበት አስተዋጽኦ | ብር = 10643 |
| 1.3 | ከብህረተሰቡ ለግንባታ የሚውል በጥሬ ገንዘብ<br>ጥሬ ገንዘቡ የሚውለው: ለአርቲዣን የጉልበት ክፍያ መጨመሪያ________<br>________________________________ | ብር = 1000 |

| ተቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 2 | የህብረተሰብ አስተዋፅኦ ከጠቅላላው የፕሮጀክቱ ወጭ ቢያንስ 15 በመቶ ያሚላል ወይ? | x | |
| 3 | በህብረተሰብ የሚቀርቡ የግንባታ ቁሳቁሶች ተፈላጊውን ጥራት ያሚላሉ?<br>________________________________<br>________________________________ | x | |

10. በግምገማ ቡድኑ ተሞልቶ ከዚህ የመገምገሚያ ፎርም ጋር በተያያዘው የዋጋ ግምት ዝርዝር መሰረት ይህ የፕሮጀክት የበጀት ማጠቃለያ መዘጋጀት አለበት፡፡

| ተቁ | የወጭ ዓይነት | ጠቅላላ ወጭ | | የማልፊ/ማትፕድርሻ | | የህብረተሰቡ ድርሻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የገንዘብ መጠን /ብር/ | % | የገንዘብ መጠን /ብር/ | % | የገንዘብ መጠን /ብር/ | % |
| 1 | የግንባታ ቁሳቁስ ወጭ | 15676 | | 4033 | | 11643 | |
| 2 | የጉልበት ወጭ | 34919 | | 33320 | | 1599 | |
| 3 | የግንባታ መሣሪያዎች ወጭ | 2775 | | 2775 | | | |
| 4 | አስተዳደራዊና ሌሎች ተዛማጅ ወጭዎች | 2006 | | 2006 | | | |
| | ድምር | 55376 | 100 | 39359 | 76.11 | 13242 | 23.89 |

ማሳሰቢያ፡- 1. ከላይ የተጠቀሰውን የፕሮጀክት ማጠቃለያ የሚደግፍ /የሚያሳይ/ የእያንዳንዱ የወጪ ዓይነት የዋጋ ግምት ከዚህ የግምገማ ዉጤት ጋር በታዩት አዝሎች መያያዝ/መሞላት አለበት፡፡

2. ከፕሮጀክቱ ባህሪ የተነሳ የጥናትና ዲዛይን ሪፖርት /ዶክመንት/ ካለው ከዚህ ሪፖርት ጋር መያያዝ ሲኖርበት የፕሮጀክቱ አጠቃላይ የዋጋ ግምት የማህበረሰቡንና ከረጂ የሚጠበቀውን በመለየት በሰንጠረዡ መጠቃለል አለበት፡፡

3. ለግንባታ የሚውል በማህበረሰቡ የተዋጣ ገንዘብ ካለ መጠኑና ለየትኛው የወጭ ዓይነተ እንደሆነ ይገለጽ፡፡ **<u>ለአርቲዣን ክፍያ የሚውል ብር 1000 ከማህበረሰቡ በጥሬ ገንዘብ ተሰብስቧል፡፡</u>**

11. የመስክ ገምጋሚው ቡድን አጠቃላይ አስተያዬት፡፡ በግምገማው መሰረት የፕሮጀክት ማመልከቻው፡-

■ መጽደቅ አለበት ☐ መጽደቅ የለበትም

ለተሰጠው አስተያየት ምክንያት ይብራራ፡፡

<u>በቢሮና በመስክ ከተደረጉት ግምገማዎች ለማየት እንደተቻለው የፕሮጀክት ማመልከቻው ከማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ የበጀት ድጋፍ ለማግኘት የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላ በመሆኑና ማህበረሰቡ ከፍተኛ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ያለበት በመሆኑ የፕሮጀክት ማማልከቻው ቢጸድቅ/የበጀት ድጋፍ ቢደረግለት መልካም እንደሆነ የገምጋሚ ቡድኑ አባላት እንገልጻለን፡፡</u>

**የገምጋሚ ቡድን አባላት ስምና ፊርማ**

| <u>ስም</u> | <u>ፊርማ</u> | <u>ቀን</u> |
|---|---|---|
| 1. <u>አቶመከብብ ሰለሞን</u> | ____________ | <u>ህዳር 28/2003</u> |
| 2. <u>ወ/ሪት ሉሲት አምሳሉ</u> | ____________ | <u>ህዳር 28/2003</u> |
| 3. ____________ | ____________ | ____________ |

**በፕሮጀክት ገምጋሚ ቡድኑ የሚሞላ የዋጋ ግምት ዝርዝር (ለምንጭና እጅ ጉድጓድ) ሰንጠረዥ**

ሀ/ ከማህበረሰብ ፕሮጀክቱ ትግበራ የሚጠበቅ የበጀት ድጋፍ

ሀ.1/ የግንባታ ቁሣቁሶች መጠንና የዋጋ ግምት በተቻለ መጠን የእያንዳንዱ ቁሳቁስ ነጠላ ዋጋ እቃውን የውሃ ጣቢያው መገንቢያ ቦታ ድረስ ለማቅረብ የሚያስፈለገውን የማጓጓዣ ዋጋ መጨመር አለበት፡፡

| ተ.ቁ | የቁሳቁሱ መጠሪያ | መለኪያ | መጠን | ነጠላ ዋጋ /ብር/ | ጠቅላላ ዋጋ /ብር/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስሚንቶ | ኩን ል | 50 | 250 | 12500 | |
| 2 | አሸዋ | ሜ/ኩብ | 1 | 3000 | 3000 | |
| 3 | የወንዝ ጠጠር | ሜ/ኩብ | 1 | 3000 | 3000 | |
| 4 | 10 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር ፌሮ | ቁጥር | 4 | 200 | 800 | |
| 5 | 6 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር ፌሮ | ኪ.ግራም | 87 | 35 | 3045 | |
| 6 | 1.5 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር ቀጭን ሽቦ | ኪ.ግራም | 2 | 35 | 70 | |
| 7 | ሚስማር | ኪ.ግራም | 4 | 200 | 800 | |
| 8 | የቤት ክዳን ቆርቆሮ | ቁጥር | 5 | 35 | 175 | |
| 9 | 4 ሜትር ርዝመት፣ 20 ሳ.ሜትር ስፋትና 2.5 ሳ. ሜትር ውፍረት ያለው የፎርም ወርክ ጣውላ | ቁጥር | 2 | 200 | 400 | |
| 10 | የተቃጠለ ዘይት | ሊትር | 6 | 5 | 30 | |
| 11 | የተሟላ አፍሪዴቭ የእጅ ፖምፕ | ቁጥር | 1 | 9500 | 9500 | |
| 12 | 2 ኢንች የብረት ቧንቧ ለምንጭ | ቁጥር | | | | |
| 13 | የ ኢንች ፎሴት ለምንጭ | ቁጥር | | | | |
| 14 | ለምንጭ አገልግሎት የሚውሉ መገጣጠሚያዎች | | | | | |
| 14.1 | 2 ኢንች ጌት ቫልቭ | ቁጥር | | | | |
| 14.2 | 2 ኢንች ኒፕልስ | ቁጥር | | | | |
| 14.3 | 2 ኢንች ዩኒየን | ቁጥር | | | | |
| 14.4 | 2 ኢንች ቲ | ቁጥር | | | | |
| 14.5 | 2 ኢንች ማሬኛ | ቁጥር | | | | |
| 14.6 | 2 ኢንች ካፕሊንግ | ቁጥር | | | | |
| 14.7 | 2 ኢንች ኢልቦው | ቁጥር | | | | |
| 14.8 | የ ኢንች ካፕሊንግ | ቁጥር | | | | |
| 15 | ለቧንቧ ማሠሪያ ቃጫ | ኪ.ግራም | | | | |
| 16 | ለቧንቧ ማሠሪያ ቀለም | ኪ.ግራም | | | | |
| 17 | 3/4 ኢንች የብረት ቧንቧ | ቁጥር | | | | |
| | | | | | | |
| **ድምር** | | | | | **33320** | |

__ማሳሰቢያ፡-__

1. አንድ ቢያጆ አሸዋ ወይም የወንዝ ጠጠር 7 ሜትር ኪዩብ ይዘት ያለው ማለት ነው፡፡

2. ሠንጠረዡ ለእጅ ጉድጓድና ለምንጭ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶችን ለመሙላት እንዲያስችል ተደርጐ የተዘጋጀ ሥለሆነ የቁሣቁሶችን መጠን የምንሞላው እንደአስፈላጊነቱ ነው፡፡

ጠቅላላ የዋጋ ግምቱን ወይም ነጠላ ዋጋዎችን በተመለከተ አስተያየት ካለ፡

________________________________________

________________________________________

### ሀ.2/ ከማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ለአርቲዣያን/ለግንባታ ባለሙያ የጉልበት ዋጋ ክፍያና ሌሎች የሚጠበቁ የጉልበት ክፍያዎች

| ተቁ | ገንዘቡ የሚያስፈልግበት ክፍያ መጠሪያ | መለኪያ | ጠቅላላ የጉልበት ዋጋ ግምት /ብር/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ለአርቲዣኑ/ለግንባታ ባለሙያ የጉልበት ዋጋ | ጥቅል | 5033 |

### ሀ.3/ የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴ አስተዳደራዊ ወጪዎች

| ተቁ | ገንዘቡ የሚያስፈልግበት ክፍያ መጠሪያ | መለኪያ | ጠቅላላ ግምት /ብር/ |
|---|---|---|---|
| 1 | በግንባታ ወቅት የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴ አባላት የተለያዩ ጉዳዮችን ለማስፈጸም ወደ ወረዳና ወደ ሌሎች ከተሞች ሲንቀሳቀሱ የሚከፈል የአበልና ትራንስፖርት ወጪ | ጥቅል | 2006 |

### ሀ.4/ በአንድ የውሃ ጣቢያ ደረጃ ሊቀርቡ የሚችሉ የግንባታ መሣሪያዎች ብዛትና የዋጋ ግምት እንደሚገነባው የውሃ ጣቢያ አይነት ምንጭ ወይም እጅ ጉድጓድ እየታየ አስፈላጊው ይሞላ::

| ተቁ | የመሣሪያው መጠሪያ ስም | መለኪያ | መጠን | ነጠላ ዋጋ/ብር/ | ጠቅላላ ዋጋ/ብር/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 18 ሚሊሜትር ናይለን ገመድ | ሜትር | 100 | 13 | 1300 | |
| 2 | ባለ 4 ሚሊሜትር ናይለን ገመድ | ሜትር | 25 | 0.40 | 10 | |
| 3 | አጭር እጀታ ያለውና የተቆፈረ አፈር ማውጫ /አካፋ/ | ቁጥር | 2 | 40 | 80 | |
| 4 | ለስሚንቶ ማቡኪያ አካፋ | ቁጥር | 4 | 40 | 160 | |
| 5 | የውሃ ባሊ | ቁጥር | 4 | 40 | 160 | |
| 6 | የስሚንቶ ባሊ | ቁጥር | 2 | 40 | 80 | |
| 7 | መቆፈሪያ ዶማ | ቁጥር | 2 | 55 | 110 | |
| 8 | ሽብልቅ | ቁጥር | 3 | 45 | 135 | |
| 9 | ገሶ | ቁጥር | 2 | 35 | 70 | |
| 10 | ትልቅ መደሻ 5 ኪሎ ግራም የሚመዝን | ቁጥር | 1 | 250 | 250 | |
| 11 | ትንሽ የድንጋይ መሰባበሪያ መዶሻ 2 ኪሎ ግራም የሚመዝን | ቁጥር | 2 | 100 | 200 | |
| 12 | መሮ | ቁጥር | 2 | 35 | 70 | |
| 13 | ዲጂኖ | ቁጥር | 2 | 75 | 150 | |
| 14 | የብረት መጋዝ ምቁጭ | ቁጥር | | | | |
| | | | | | | |
| ድምር | | | | | 2775 | |

**ማሳሰቢያ**

1. አንዳንድ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና ከአንድ በላይ ለሆነ የውሃ ጣቢያ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎች /ለምሣሌ የውሃ ልክ፣ ሜትር፣መጋዝ፣ የኮንክሪት ሲሊንደር ማምረቻ ሞልድ፣ የቧንቧ ጥርስ ማውጫ፣ የቧንቧ ማሠሪያና የቧንቧ መቁረጫ/ የመሣሠሉት ዋጋቸው በፕሮጀክቱ ዋጋ ግምት ውስጥ/በመገምገሚ ቅጹ አልተካተተም እነዚህን መሣሪያዎች ለውሃ ጣቢያው ግንባታ መቅረብ የሚገባቸው ወቅት ሲደርስ የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴው ከአርቴዥያኑ ጋር በመሆን ከወረዳው የውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት መዋስ ይችላሉ::

ጠቅላላ የዋጋ ግምት ወይም ነጠላ ዋጋዎችን በተመለከተ አስተያየት ካለ

______________________________________________

______________________________________________

## ለ/ የማህበረሰቡ /በህብረተሰቡ/ ተሳትፎ ስለሚሸፈኑ ዋጋዎች ዝርዝር

### ለ.1/ በማህበረሰብ ተሳትፎ የሚቀርቡ የግንባታ ቁሣቁሶች መጠንና የዋጋ ግምት

| ተ.ቁ | የቁሣቁሱ አይነት | የአካባቢው መለኪያ | የቁሳቁሱ መጠን | ነጠላ ዋጋ /ብር/ | ጠቅላላ ዋጋ /ብር/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ድንጋይ | ሜ.ኩብ | 12 | 75 | 900 | |
| 2 | አሸዋ /ጥራቱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ ነው/ | ቢያጆ | - | - | - | |
| 3 | የወንዝ ጠጠር /ጥራቱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ ነው/ | ቢያጆ | - | - | - | |
| 4 | ለውሃ ጣቢያው አጥር ማጠሪያ የሚውል ንጨት | ቁጥር | 52 | 12 | 624 | |
| 5 | ለስሊንደር ማስገቢያ የሚውሉ ወፍራም ግንዲላ እንጨቶች | ቁጥር | 3 | 25 | 75 | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | | | **1599** | |

### ለ.2/ የማህበረሰቡ የጉልበት አስተዋፅኦ ወደ ገንዘብ ሲለወጥ

| ተ.ቁ | ማህበረሰቡ የሚሳተፍበት የጉልበት አይነት | መለኪያ | መጠን | ነጠላ ዋጋ /ብር/ | ጠቅላላ ዋጋ /ብር/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግንባታን ለማከናወን የሚደረግ ተሳትፎ | የሰው ቀን | **44** | **20** | **8800** | |
| 2 | የግንባ ቁሣቁስና መሣሪያዎችን ለማጓጓዝ የሚደረግ ተሳትፎ | የሰው ቀን | 55 | 25 | 1375 | |
| 3 | የግንባታ ቁሳቁሶችን ማከማቻ መጋዝን በማቅረብና መሣሪያዎችን ለመጠበቅ የሚደረግ ተሳትፎ | ወራት | 10 | 20 | 200 | |
| 4 | በየቀኑ የሚሠራውን የግንባታ ሂደት ለመመዝገብ የሚመደብ የዋ.ሽ.ኮ አባል ተሳትፎ | የሰው ቀን | 2.5 | 75 | 188 | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | | | **10643** | |

# 2.4

# የፕሮጀክት ማመልከቻዎችን ማጽደቅ (Approval of project application or Decision of the Woreda WaSH Team/WWT)

## 2.4. የፕሮጀክት ማመልከቻዎችን የማጽደቅ (Approval of project application or Decision of the Woreda WaSH Team/WWT)

### 2.4.1. የፕሮጀክት ማመልከቻዎች የመጨረሻ ውሳኔ በማን ይሰጣል ?

- ለማ.ፐ.ት የበጀት ጥያቄ ቀርበው በቢሮ እና በመስክ ደረጃ ግምገማዎችን ያለፉ ማመልከቻዎች የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙት በወረዳው የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ቡድን /ዋሽ ቲም/ ነው።

- የወረዳው ዋሽ ቡድን ተጠሪነቱ ለወረዳው ካቢኔ ሁኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።
  - የወረዳው አስተዳዳሪ (የቡድኑ ሰብሳቢ)
  - የወረዳው ውሀ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው ገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው ግብርና ልማት ዋና ጽ/ቤት ሀላፊ
  - የወረዳው የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪ (የቡድኑ ጸሀፊ) ???
    - የወረዳው አስተዳዳሪ በተለያዩ የስራ ምክንያቶች የሰብሳቢነቱን ሀላፊነት ውክልና የሚሠጥ ከሆነ ውክልናው ለውሃ ወይም ለጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሃላፊ ይሰጥና የወረዳው አስተዳዳሪ አስተዳደሩን የሚወክል ሌላ አባል ይተካል።

- የወረዳው ማ.ፐ.ት ተቆጣጣሪ ከወረዳው የውሀ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የሚመረጥ ባለሙያ ሲሆን በወረዳው ስለ ማ.ፐ.ት አሰራር አብዛኛውን ሀላፊነት ሊወጣ የሚችል ባለሙያ ነው።

- አንድ የማ.ፐ.ት ፕሮጀክት ማመልከቻ ለበጀት ድጋፍ ተቀባይነት የሚኖረው ቢያንስ የሚከተሉት የቡድኑ አባላት ካጸደቁት ነው።
  - የዋሽ ቡድኑ ሰብሳቢ
  - የወረዳው የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪ
  - ሌሎች ሶስት /3/ የቡድን አባላት። ????

- ቡድኑ ለፕሮጀክቶች የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ስብሰባ ላይ ነው፡፡

- የቡድኑ ፀሀፊ የቡድኑ አባላት ፕሮጀክቱን ውሣኔ የሚሰጡበትን ቅፅ ከመስክ ደረጃ ገምጋሚው ቡድን ጋር በመሆን ያዘጋጃል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክቱን መረጃ የያዘ ፋይል ከማፅደቂያ ቅፁ ጋር በማድረግ የቡድኑ ስብሰባ ላይ ይዞ ይቀርባል፡፡

- ከተቻለና ግዜ ካለ የቡድኑ አባላት ከስብሰባው በፊት የተዘጋጀውን የፕሮጀክት ፋይል ቀድመው እንዲያዩት ማድረግ ይቻላል፡፡

- የቡድኑ  ውሳኔ መስጫ ቅጹን ይዘት በማ.ፐ.ት የትግበራ መመሪያ <u>በቅጽ ዝ.10</u> ላይ ይመልከቱ፡፡

- በማጽደቂያው ስብሰባ ላይ የወረዳው ማ.ፐ.ት ተቆጣጣሪ ለቡድኑ አባላት ስለማመልከቻው ይዘትና ሥለግምገማው ውጤት አንዳንድ ማብራሪያዎችን በመስጠት ወይም አባላቱ የፕሮጀክት ፋይሉን እንዲመረምሩ በማድረግ የውሳኔ ሀሣብ እንዲሰጡበት ያደርጋል፡፡ ውሳኔውንም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቅፅ ላይ ፊርማቸውን በማሳረፍ ይገልጻሉ፡፡

- የማ.ፐ.ት አሰራር በወረዳው ተግባራዊ በሚደረግባቸው በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ቡድኑ ቢያንስ በየ 15 ቀኑ  የተሰበሰበ በፕሮጀክት ማመልከቻዎች ላይ እና ሌሎች ከአሰራር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 2.4.2 የወረዳው ዋሽ ቡድን የፕሮጀክት ማመልከቻዎችን የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ምን ምን ጉዳዩች ላይ ማተኮር አለበት ?

- ቡድኑ ማመልከቻው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት ከፕሮጀክት ፋይሉም ሆነ ከማ.ፐ.ት ተቆጣጣሪ ከሚሰጠው ማብራሪያ በመነሳት ቢያንስ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማተኮር አለበት፡-
    - በፋይሉ ውስጥ በአግባቡ የተሞላ የፕሮጀክት ማመልከቻ ቅጽ መሮሩን፣
    - በፋይሉ ውስጥ በአግባቡ የተሞላ የፕሮጀክቱ የቢሮና የመስክ ደረጃ ግምገማ ቅጽ መሮሩን፣
    - ፕሮጀክቱ በማ.ፐ.ት የበጀት ድጋፍ ሊሰጣቸው ከሚችሉት የውሃ ጣቢያዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን፣

- ተጠቃሚው ማህበረሰብ የቅድሚያ የገንዘብ መዋጮ በማሰባሰብ በውሃ ጣቢያው ስም በወረዳው ብድርና ቁጠባ ተቋም ንኡስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ ማድረጉንና ይህንን የሚያሳይ ደረሰኝ ከፕሮጀክቱ ፋይል ጋር መያያዙን ፣
- ለግንባታ ስራ የሚውለው ከህብረተሰቡ የሚዋጣው የገንዘብ፣ የጉልበትና የግንባታ ቁሳቁስ አስተዋጽዎ ቢያንስ የፕሮክቱን የግንባታ ዋጋ የማህበረሰብ ከሆነ 15 % የተቋም ከሆነ 6 % መሆኑን፣
- ለግንባታ ስራ የሚውለውና በእርዳታ የሚሰጠው /የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ድርሻ/ የገንዘብ መጠን ቢበዛ የፕሮክቱን ግንባታ ዋጋ ግምት የማህበረሰብ ከሆነ 85 % የተቋም ከሆነ 94% ?? ብቻ መሆኑን፣
- ለግንባታ ስራ የሚውለውና የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ድርሻ የገንዝብ መጠን በፕሮጀክቱ ድጋፍ ሊደረግ የሚችለው ትልቁን የበጀት ጣሪያ (Critcal maximum cost) የተቀመጠ ከሆን ይህን አለመብለጡን፣
- የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ አባወራ ቁጥር ከ 50 በታች ሁኖ ነገር ግን ማመልከቻው ተቀባይነት (Approval) እንዲያገኝ በገምጋሚው ቡድን ሀሳብ ከቀረበ ለዚህ የተሰጠው ምክንያት ምን ያህል አጥጋቢ እንደሆነ ማረጋገጥ ይገኙበታል::

## ማሳሰቢያ

- የአንድን ፕሮጀክት የመጽደቅ እጣ ፋንታ ከሌላ ተመሳሳይ ፕሮጀክት ጋር በምናወዳድርበትና ዉሳኔ በምንሰጥበት ወቅት ተጠቃሚው ማህበረሰብ የቅድሚያ በሚያዋጣው ገንዘብ ብቻ መታየት የለበትም:: ህብረተሰቡ ያለበት የመጠጥ ውሃ ችግር አንገብጋቢነት ግምት ውስጥ መግባት አለበት:: ይህም የሚሆነው በአንፃራዊነት ብዙ ገንዘብ የማዋጣት አቅማቸው አነስተኛ የሆኑ ማህበረሰቦችን ከተጠቃሚነት ላለማግለል ነው::

## 2.4.3 ከወረዳው ዋሽ ቡድን የፕሮጀክት ማመልከቻውን በተመለከተ ምን ምን ዓይነት ውሳኔዎች ይጠበቃሉ ?

- ለወረዳው ዋሽ ቡድን የመጨረሻ ውሳኔ የቀረበው የፕሮጀክት ማመልከቻ በተመለከተ ቡድኑ ከሚከተሉት 3 /ሦስት/ አማራጮች አንዱ ሊወሰን ይችላል::
    1. ለማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ የበጀት ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘት(Approval) ፣
    2. ለማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ የበጀት ድጋፍ ተቀባይነት አለማግኘት (Rejection)፣

3. የማመልከቻውን ተቀባይነት የማግኘት ወይም ያለማግኘት ውሳኔ ለሌላ ጊዜ ማሸጋገር (Suspended or deffered) ሊሆኑ ይችላሉ:: በዚህ ውሳኔ ወቅት ውሣኔው ስከመቼ እንደተሸጋገረ በስብሰባው ወቅት በሚያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ መስፈር አለበት::

- የኘሮጀክት ማመልከቻው ላይ ውሣኔ ለሌላ ግዜ እንዲሸጋገር ለማድረግ ውሣኔ ላይ ሊያደርሱ የሚያስችሉ የተለያዩ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሣሌ ያህል:-
  1. በቡድኑ አባላት አስተያየት የፕሮጀክት ማመልከቻው ወይም ግምገማው በደንብ ያላካተታቸውና እንደገና መታየት የሚገባቸው ሁኔታዎች ካሉ እንደገና እንዲታዩ ሲያስፈልጉ፣
  2. ለአመቱ ለወረዳው የተመደበው የማ.ፕ.ት በጀት ከዚህ በፊት ዉሳኔ ላገኙ ፕሮጀክቶች ሙሉ ለሙሉ ከተመደበና ለጊዜው ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚሆን በቂ በጀት ወረዳው ከሌለው ይህ የበጀት ጉዳይ እልባት አስኪያገኝ ድረስ::
- ለማ.ፕ.ት የበጀት ድጋፍ ተቀባይነት ያላገኙና ውሳኔያቸው ለሌላ ግዜ የተላለፉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ለአመልካቹ ማህበረሰብ በቡድኑ የተወሰነውን ውሣኔ ከነምክንያቱ የሚገልጽ ደብዳቤ በቡድኑ ሰብሳቢ ይጻፍላቸዋል ::
- በቡድኑ ውሣኔ መሠረት ከማ.ፕ.ት የበጀት ድጋፍ እንዲደረግላቸው የተወሰነላቸው ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ለውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴው ሰብሳቢ ይህ ሁኔታ ተጠቅሶ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ማመልከቻ አወንታዊ ምላሽ ማግኘትን /መጽደቅን/ ለአመልካቾች ማሳወቂና የገንዘብ ውል ስምምነት ለመፈራረም ጥሪ ደብዳቤ <u>በቅጽ ዝ.11</u> ይጻፍላቸዋል::
- የወረዳው ዋሽ ቡድን አባላት ፕሮጀክቶች በግምገማ ውጤት በተለይ በመሥክ ግምግማ የተነሣ ለማ.ፕ.ት የበጀት ድጋፍ ተቀባይነት የማያበቁ የግምገማ ውጤቶት ላይ በቂ ግንዛቤ እስኪኖራቸው ድረስ የገምጋሚው ቡድን አባላት ለቡድኑ አባላት በግምገማ ምክንያት ተቀባይነት እንዳያገኙ የሚወስንባቸውን ፕሮጀክቶች ሁኔታ ማብራሪያ /ገለፃ/ ቢያደርጉ ጥሩ ይሆናል::
  - ወደፊት ግን /በቂ ግንዛቤ ማግኘታቸው ሲታመንበት/ በመስክ ገምጋሚው ቡድን ውጤት መሰረት ለአመልካቹ ማህበረሰቡ የፕሮጀክቱን ተቀባይነት አለማግኘት በቡድኑ ሰብሳቢ ደብዳቤ አንዲጻፍለት ብቻ ማድረግ ይበቃል::
- ለናሙናነት የተዘጋጀውን የማህበረስብ ፕሮጀክት ትግበራ ማመልከቻ የመጨረሻ ውሳኔ መስጫ ቅጽ በዚህ ማንዋል <u>በቅጽ ዝ.10</u> ላይ ይመልከቱ::
- የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ማመልከቻ አወንታዊ ምላሽ ማግኘትን /መጽደቅን/ ለአመልካቾች ማሳወቂያና የገንዘብ ውል ስምምነት ለመፈራረም የጥሪ ደብዳቤ ይዘትን በዚህ የስልጠና መመሪያ በ ዝል <u>በቅጽ ዝ.11</u> ላይ ይመልከቱ::

# ቅፅ - ዝ.10

## የወረዳው ዋሽ ቡድን የፕሮጀክቶች ማጽደቂያ ቅፅ

**1. የፕሮጀክቱ ማጠቃለያ**

ሀ. የፕሮጀክቱ መጠሪያ/ስም: <u>የልጀ ንጉስ እጅ ጉድጓድ ግንባታ</u>

ዞን : <u>ምዕራብ ጎጃም</u> ቀበሌ : <u>ንጉስ</u>

ወረዳ : <u>ደጋ ዳሞት</u> ጎጥ : <u>ልጀ ንጉስ</u>

ለ. የውሃ ጣቢያው ዓይነት

የእጅ ጉድጓድ ■ ምንጭ በቦታው ከለማጠራቀሚያ ጋን ☐

ምንጭ በቦታው ከነማጠራቀሚያ ጋን ☐ ሌላ /ይገለጽ/ ____________________

ሐ. ጠቅላላ የፕሮጀክቱ ወጭ ግምት <u>55376</u> ብር

መ. የማ.፻.ት ድርሻ <u>39359</u> ብር

- የማ.፻.ት ድርሻ ከጠቅላላው የፕሮጀክት ወጪ <u>23.89</u> በመቶ ይሆናል::

ሠ. የተጠቃሚዎች ብዛት

- አባወራ/ ማውራ : <u>55</u>
- ጠቅላላ : <u>270</u>
  - ወንድ : <u>132</u> ሴት : <u>138</u>

**2. የፕሮጀክቱ አስፈላጊነትና የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

ሀ. በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

**1. 1.5 ሜትር ዲያሜትርና 15 ሜትር ጥልቀት የሚኖረው የእጅ ጉድጓድ መቆፈርና መገንባት:**

**2. አፍሪደቭ የእጅ ፓምፕ መትከል::**

**3. ጉድጓዱን በክሎሪን ማከምና ዙሪያውን ማጠር::**

**4. ለልብስ ማጠቢያ የሚሆን ሲሊንደር ማዘጋጀት::-----------------------------------**

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

ለ. በገምጋሚ ቡድኑ ስለፕሮጀክቱ አስፈላጊነት የቀረበ አስተያየት/ማረጋገጫ

<u>የፕሮጀክት ማመልከቻው ከፍተኛ የሆነ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ያለባቸውን 270 ሰዎች እንዲያገለግል በራሳቸው ተነሳሽነት የቀረበ ነው:: ማህበረሰቡ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ጉልበት፣ የግንባታ ቁሳቁስና ገንዘብ ውስጥ አቅሙ የፈቀደውንና ሊያደርግ የሚችለውን ለማድረግ ቃል ገብቷል:: እንዲሁም በተጨማሪ የፕሮጀክቱን ዘላቂነት</u>

<u>ለማረጋገጥ ስፈላጊ የሆነውን አጠቃቀምና ጥገና ወጪ ለመሸፈን ዝግጁቱን ጀምሯል:: ስለዚህ ከላይ የቀረቡት ሁኔታዎች ማህበረሰቡ ፕሮጀክቱ በጣም እንደሚያስፈልገውና ዘላቂ ሊያደርገው የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ስለሚጠቁሙ የፕሮጀክቱ ሃሳብ ተቀባይነት ቢያገኝና ግንባታው ቢከናወን በጣም ወሳኝ ነው እንላለን::</u>

**3. የወረዳ ዋሽ ቡድን/ቲም ውሣኔ**

☒ ፀድቋል

☐ አልፀደቀም

☐ ውሳኔው ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ተወስኗል

የፕሮጀክቱ አለመጽደቅ ወይም ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ የተወሰነበት ምክንያት

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

**የወረዳው ዋሽ ቡድን አባላት ስምና ፊርማ**

| የወረዳው ዋሽ ቲም አባል ስም | በቡድኑ የሥራ ድርሻ | የወከለው መ/ቤት | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| አቶ ሉሉ አሰፋ | ሰብሳቢ | ወረዳ አስተዳደር | | |
| አቶ መከተ ሙሉነህ | አባል | ው.ሀ.ል ጽ/ቤት | | |
| አቶ ጋሻው በዛ | አባል | ጤና ጽ/ቤት | | |
| አቶ ሹመት አሊ | አባል | ትምህርት ጽ/ቤት | | |
| አቶ ሞላ ባለው | አባል | ገ.ኢ.ል ጽ/ቤት | | |
| አቶ ተን ጋሹ | አባል | ግብርና ጽ/ቤት | | |
| ወ/ሮ ሙሉ ወሌ | አባል | ሴ.ህ.ወ ጽ/ቤት | | |
| አቶ መክብብ ሰለሞን | ፀሐፊ | ማ.ፐ.ት ተቆጣጣሪ | | |

ይህ ቅጽ የዋሽ ቡድኑ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት በዋሽ ቲሙ ፀሐፊና የገምጋሚ ቡድኑ አባላት በጋራ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል::

**ቅጽ- ዝ.11.** የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ማመልከቻ አወንታዊ ምላሽ ማግኘትን/መፅደቅን/ ለአመልካቾች ማሳወቂያና የገንዘብ ውል ስምምነት ለመፈራረም መጥሪያ ወረቀት/ደብዳቤ

(Informing approval of a water point project application & call for signing of funding agreement)

ቀን: _____________________

ቁጥር: ____________________

ለአቶ/ወይዝ. ትርንጎ ባይህ የ ልጀ ንጉስ ጎጥ
ውሃ ጣቢያ የውሃ ንፅህናና ሀይጅን ኮሚቴ ሰብሳቢ

ጉዳዩ: መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ማመልከቻ መፅደቁን ማሳወቅና የገንዘብ ውል ስምምነት የመፈራረም ጥሪን ይመለከታል

ለ ልጀ ንጉስ ጎጥ የመጠጥ ውሃ ግንባታ ያቀረባችሁት የፕሮጀክት ማመልከቻ ተቀባይነት ማግኘቱንና ከማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ብር 35000 /ሰላሳ አምስት ሺህ ብር/ ብቻ የፀደቀላችሁ መሆኑን ስንገልጽ ደስታ ይሰማናል:: የጸደቀውም የውሃ ጣቢያ ፕሮጀክት ዓይነት የእጅ ጉድጓድ ግንባታ ነው::

ስለዚህ ከፀደቀው በጀት የመጀመሪያውን ክፍያ ማስተላለፍ ከመጀመራችን በፊት የሚከተሉትን ወሳኝ ሁኔታዎች እንድታሟሉ እንጠይቃለን::

1. የውሃ ንፅህናና ሀይጅን ኮሚቴው ሰብሳቢና ገንዘብ ያዥ ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው ቢበዛ በ 7/ሰባት/ ቀናት ውስጥ በወረዳው የውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የሚሰራውንና የወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪን አቶ/ወይዝ. መክብብ ሰለሞንን በማግኘት በፕሮጀክቱ ስም በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ንዑስ ቅ/ጽ/ቤት የሂሳብ ቁጥር ለመክፈት የሚያስችላችሁን ደብዳቤ ንድትቀበሉ::
2. ከወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪ የምትቀበሉትን ደብዳቤ በመጠቀም በቁጠባ ተቋሙ የፕሮጀክቱን ማመልከቻ በም ቀርቡበት ወቅት ከህብረተሰቡ የተዋጣውን ገንዘብ ለማስቀመጥ ከከፈታችሁት የቁጠባ ሂሳብ የተለየ ሌላ የሂሳብ ቁጥር እንድትከፍቱና የተከፈተውን የማጠራቀሚያ ሂሳብ ስም ቁጥርና የፈራሚዎችን ስም በቃል ወይም በደብዳቤ ለወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪ አቶ/ወይዝ. መክብብ ሰለሞን ወዲያውኑ እንድታሳውቁ::
3. በዚሁ ጊዜ ከወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪ ዘንድ የገንዘብ ውል ስምምነቱ መቼና የት እንደሚፈረም መረጃ/ቀጠሮ/ መውሰድ ይኖርባችኋል::

የማጠራቀሚያ ሂሳብ ቁጥሩ ከተከፈተና የውል ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ የወረዳው ዋሽ ቡድን ለፕሮጀክቱ ከፀደቀው ገንዘብ ውስጥ የመጀመሪያውን ክፍያ በሂሳብ ቁጥራችሁ ገቢ እንደሚያደርግላችሁ እናስታውቃለን::

ከሠላም ጋር

የወረዳው ዋሽ ቡድን ሰብሳቢ

ግልባጭ//

- ከፕሮጀክት ፋይሉ ጋር የሚያያዝ